ቀን:- 23/11/2015 ዓ/ም

# ማስታወቂያ

## ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሙሉ

አክሱም ዩኒቨርሲቲ በጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የመማር ማስተማር ስራውን ለማስቀጠል ሲያደርገው የነበረውን ዝግጅት ማጠናቀቁን እየገለፅን ቀጥሎ በተቀመጠው መርሀ-ግብር መሰረት ማለትም፡

1) 3ኛ ዓመትና ከዚያ በላይ የነበራችሁ መደበኛ(Regular) የቅድመ-ምረቃ ተማሪዎች፣ ሁሉም የሕክምና ትምህርት ክፍል (Medicine department) ተማሪዎች እና ሁሉም መደበኛ የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ነሐሴ 2 እና 3 ቀን 2015 ዓ/ም ፤

2) ሁሉም የክረምት(Summer) ቅድመ-ምረቃና ድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ነሐሴ 4 እና 5 ቀን 2015 ዓ/ም፤

3) ሁሉም የኤክስቴንሽን (Extension) ቅድመ-ምረቃና ድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ነሐሴ 6 እና 7 ቀን 2015 ዓ/ም፤

4) 1ኛና 2ኛ ዓመት የነበራችሁ መደበኛ(Regular) የቅድመ-ምረቃ ተማሪዎች መስከረም 10 እና 11 ቀን 2016 ዓ/ም፤

5) በትግራይ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ውጪ ተመድባችሁ የመሄድ ዕድል ያላገኛችሁ ወይም ትምህርታችሁን ያቋረጣችሁ ተማሪዎች አስፈላጊ የትምህርት ማስረጃዎቻችሁን በመያዝ ከላይ በቁጥር 1 እስከ 4 በተገለፀው መሰረት

በየተመደበላችሁ ግቢ በአካል በመገኘት እንድትመዘገቡ እናሳውቃለን።



CamScanner

## ሪፖርት የምታደርጉበት ግቢ፥

- ከሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ተማሪዎች በስተቀር ሁሉም የዋና ግቢ ተማሪዎችና የዓድዋ ግቢ ተማሪዎች በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ
- የጤና ሳይንስ ግቢ ተማሪዎችና ሁሉም መደበኛና ክረምት የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ ተማሪዎች በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ግቢ
- የአክሱም ዩኒቨርሲቲ ሽረ ግቢ ተማሪዎች በሽረ ግቢ

ማሳሰቢያ፡

1. ከተጠቀሰው ቀን ቀድሞም ሆነ ዘግይቶ ለሚመጣ ተማሪ ዩኒቨርሲቲው ኣያስተናግድም።
2. መደበኛ የቅድመ-ምረቃ ተማሪዎችና ሁሉም የክረምት ተማሪዎች አንሶላ፣ ብርድ ልብስና የትራስ ጨርቅ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቿል።
3. ሁሉም የክረምት ተማሪዎች መገጣጠምያ(የድጋፍ ደብዳቤ) ይዘው መምጣት አለባቸው።

የአክሱም ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ፅ/ቤት